ወደ መዳን
የሚያደርስ እውነት



Scanned by CamScanner

ይህች በጥቂት ገጾች ተዘጋጅታ ለንባብ የቀረበች በራሪ ጽሁፍ(በክሊት) ህይወት የሚገኝበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በውስጥዋ የያዘች ስለሆነ በጥሞና (በማስተዋል) እንዲያነቧት እንጋብዛለን ::

በ1ኛ ጢሞ. 2÷3-4 እንደተፃፈው እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ይፈልጋል። በዚህም መሠረት ወደ መዳን የሚያደርሰንን ትምህርትና የራሱን ማንነት ምሥጢር በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንድንመለከተው አድርጎአል:: የእግዚአብሔር ማንነትና የመዳን አሰራር መንገዱ ሳይታወቅ የዘላለም ሕይወት ማግኘት ከቶ አይታሰብም (ዮሐ. 17÷3፣1ኛዮሐ.5÷20-21):: ማንነቱን ሳያውቁ በመላና በጭፍን እምነት አለኝ ማለትም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የለውም:: ስለሆነም ቀጥሎ የቀረቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ የመዳን ትምህርቶች አስተውለው እንዲያነቡ በድጋሚ አደራ እንላለን ::

1. መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የተፃፈ፣ ምንም ስህተት የሌለበት፣ እግዚአብሔር የሰው ልጆች ሁሉ ይድኑበትና ይመሩበት ዘንድ የሰጠው እውነተኛ መጽሐፍ ነው:: ይህ መጽሐፍ የመዳንን መሠረታዊ ትምህርት የያዘ፣ በራስ እውቀት መተርጎም ያልተፈቀደ፣ የቃሉ ምስጢር የተገለጠላቸው የእምነት አባቶች (ነቢያትና ሐዋርያት) ባስተማሩት ትምህርት ወይም ስብከት ላይ እምነታችንን መመስረት እንደሚገባን የሚያስተምር ቅዱስ መጽሐፍ ነው ::
የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመልከቱ: 2ኛ ጴጥ.1÷20-21 ፣ ዘዳ. 8÷3 ፣ ኢሳ. 34÷16፣ መዝ. (12)÷6፣መዝ. (119) ÷ 89፣ ሮሜ 10÷17 ፣ 2ኛ ጢሞ. 4÷3 ፣ ራዕ. 1÷3 ፣ ራዕ. 22÷18-19)

2. አንድ አምላክ

በዘዳ.6÷4 እና ማር.12÷29-34 እንደተፃፈው "ፈጣኝይቱ ትዕዛዝ እግዚአብሔር አንድ ነው" የምትል ናት:: የመጀመሪያው ትዕዛዝ ላይ እምነት ከተፋለሰ ቀጣዩ የእምነት ጉዞ በሙሉ የተፋለሰ ይሆናል:: ይህ እንዳይሆን እግዚአብሔር አምላክ በሲና ተራራ አንድ አምላክ ብቻ መሆኑን ካወጀ በኋላ በቀጣይነት በዘፀ. 22÷20 "ከእግዚአብሔር በቀር ለአንዳች አምላክ የሚሰዋ ፈጽሞ ይጥፋ " በማለት በዘዳ. 4÷34-39 ፣ በዘዳ. 5÷6-10 ፣ በዘዳ. 6÷4 ፣ በዘዳ. 32÷39 ላይ ብቻውን የሆነ አንድ አምላክ መሆኑ በተደጋጋሚ አጠንክሮ ተናግሮአል ::

Scanned by CamScanner

ወደ ነቢያት ዘመንም ሲመጣ ያው የአባቶች አንድ አምላክ ሳይለወጥ በነቢያቱ አፍ "ብቻዬን ያለሁ አምላክ ነኝ .... ማንንም አላውቅም " በማለት እንደተናገረ እነዚህ ጥቅሶች ያስተምራሉ:: (ኢሳ. 44÷6-8 ፣ ኢሳ. 45÷5-7 ፣ ኢሳ. 45÷21-22 ፣ ኢሳ 46÷8-10 ኢሳ. 48÷12-13)::

በኢሳ.40÷12-14 ላይ እግዚአብሔር ያማከረው ወይም የተመካከረው ሌላ እንደሌለው አረጋግጦአል:: በተመሳሳይ በኢሳ.44÷24-26 እንደተጸፈው እግዚአብሔር ያለ አማካሪ ማንም አጠገቡ ሳይኖር ለብቻው ፍጥረታትን እንደፈጠረ ቃሉ ያስተምራል ::

በኢሳይያስ 43÷10-13 እንደተፃፈው እግዚአብሔርን የቀደመ ወይም ከእርሱ በኋላ የተሰራ ሌላ አምላክ አለመኖሩን እያስረገጠ "እኔ÷እኔ እግዚአብሔር ነኝ " ይላል:: እንደዚሁ በኢሳ.44÷6-8 ላይ የበለጠ አጠንክሮ በፊትም ሆነ በኋላ ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ እንዳልነበረና እንደማይኖር ይናገራል ::

መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው አምላክ አንድ መሆኑን እየደጋገመ ከመናገር አልፎ ሌላ ተደራቢ እንዳይቀጠልበት "ብቻውን " በሚል የማሰሪያ ቃል በማያያዝ የማይነቃነቅ አድርጎታል (ነህ. 9÷6 ፣ ኢዮ. 23÷13 ፣ ዘዳ. 32÷39 ፣ 2ኛ ነገ. 19÷19 ፣ ኢሳ. 37÷20 ፣ ዮሐ. 17÷3 ፣ 1ኛ ጢሞ. 1÷15-17 ፣ 1ኛ ጢሞ. 6÷15 ይሁዳ ቁጥር 4 ቁጥር 25)::

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አንድ አምላክና አንድ አባት እንደሆነ ከእርሱም በቀር ሌላ እንደሌለ በሰፊው የሚያስተምር ሲሆን ከአንድ የሚበዙ የአምላክ አካላት በጋራ ፍጥረታትን እንደፈጠሩ አድርገው ለሚያስቡ የሚከተሉት ጥቅሶች በቂ መልስ ይሰጣሉ (ሚል. 2÷10 ፣ ዘካ. 14÷9 ፣ ኢሳ. 9÷6 ፣ 1ኛ ቆሮ. 8÷6 ፣ ገላ. 3÷20 ፣ ኤፌ. 4÷4-6 1ኛ ጢሞ. 2÷5 ፣ ያዕ. 2÷19 ፣ ኢሳ. 44÷24-25 ፣ ኢሳ. 45÷12 ቁ 19 ፣ ሮሜ 11÷33-36 ፣ኤፌ.1÷11 ፣ራዕ.1÷4-5)::

3. እግዚአብሔር አንድ ብቻ ከሆነ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ምንድን ናቸው?

የተለያዩ የሃይማኖት ትምህርቶች በአሁኑ ዘመን በተለይም በክርስትናው ዓለም የብዙዎች ችግር ሆነው ትልቅ መለያየትን ሲፈጥሩ:- "አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ሦስት ናቸው፤ አንድም ሦስትም ናቸው ፤ በአካል፣ በግብር፣ በስም ሦስት ናቸው ፤ አይደለም አንድ ናቸው፤ ወዘተ... በማለት ትውልዱ እጅግ ግራ እንዲጋባ እያደረጉ

Scanned by CamScanner

ይገኛሉ:: ሆኖም እውነተኛውን ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ እንደሚከተለው እናገኛለን ::

ሰው አንድ ሆኖ እያለ መንፈስ ነፍስና ሥጋ ያለው ፍጡር እንደሆነ ሁሉ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ መገለጡን ያሳያሉ :: ይህም ማለት እንደ አባት በፈጣሪነት እንደ ልጅ በዘመን ፍፃሜ ሰዎችን (ኃጢአተኞችን) ለማዳን በሥጋ መገለጡን ፤ እንደ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ለማደስና ለመቀደስ ከመንፈሱ እያካፈለን እንደተገለጠ ቃሉ ያስተምረናል፤ ይህንንም እውነት በዝርዝር መመልከት ተገቢ ነው ::

3.1. እግዚአብሔር አብ

እግዚአብሔር አብ የነበረ ያለና የሚኖር፣ ፍጥረታትን ሁሉ ለብቻው የፈጠረ የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ አምላክና አባት ነው:: እግዚአብሔር አብ መንፈስ የሆነ፣ ሰማይንና ምድርን የሞላ፣ ይህን ይመስላል ተብሎ በአካል አምሳያ ምስል ወይም ሰዕል የማይሳልለት፣ የማይሞት፣ ከዘላለም እስከዘላለም ሕያው የሆነ፣ ማንም ሰው ያላየውና ሊያየውም የማይቻለው፣ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን የሚኖር፣ የማይዳሰስ፣ በሁሉ ሥፍራ የሚገኝ ወይም በሥፍራ የማይወሰን መንፈስ የሆነ አምላክ ነው ::

ሚል. 2÷10 "ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን::" ይላል:: ፩ኛ ቆሮ. 8÷6 "ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን "::

ኤፌ.4÷6-7 "ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ"

ማቴ. 6÷9 "እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡- <u>በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ</u> ስምህ ይቀደስ ...."

ማቴ. 23÷9 "አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና ..... ሊቃችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ ነውና"

• የሚከተሉትን ጥቅሶች በተጨማሪ እናጥና

ዮሐ. 4÷24፣ ኤር.23÷23-24፣ዘዳ.4÷12-19፣ ፩ኛጢሞ.6÷14-16፣ ዮሐ.1÷18፣መዝ.(139)÷7-8፣ ኢሳ.66÷1-2፣ ፩ኛነገ.8÷27፣ ዮሐ.3÷13 ፣ሉቃ.24÷39 ፣ ዮሐ.1÷1-12)

Scanned by CamScanner

3.2. ወልድ /የእግዚአብሔር ልጅ/

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስሞችን ለማዳን የተገለጠበትን የሥጋ ሰውነት ወልድ፣ ክርስቶስ ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ ይጠራዋል። ክርስቶስ ኢየሱስ በመለኮትነቱ (በመንፈሱ) ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ ብቸኛ አምላክ ሲሆን በሥጋ ሰውነቱ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ሮሜ.9÷5፣2ኛቆሮ.5÷19፣ቆላ.1÷22)። ወልድ ከመወለዱ በፊት በአብ ውስጥ የነበረ የአብ የራሱ ቃል እንደሆነና እግዚአብሔር ስሜይንና ምድርን ፍጥረታትንም ሁሉ የፈጠረበት ቃሉ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ወልድ ከአብ በተለየ በራሱ አካል የኖረበት ጊዜ የለም፤ አይኖርምም። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና የአብ ቃል በማርያም ማህፀን አድሮ በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ምድራዊ ዘር ያልተቀላቀለበት ሰማያዊ ሥጋ ሆኖ እንደታየ ወይም እግዚአብሔር በሥጋ እንደተገለጠ ቃሉ ያስተምረናል። የማይታየው መለኮት (አብ) በሚታየው ሰውነት በክርስቶስ (በልጁ) ተገለጠ ። የእግዚአብሔር ቃል ሥጋ ሆኖ ተወልዷልና በስጋው ሰውነት የእግዚአብሔር ልጅ ተባለ። እግዚአብሔር ሥጋን በማዘጋጀት ወይም በሥጋው ሰውነት (በክርስቶስ) ከራሱ ጋር አስታረቀን። (2ኛ ቆሮ.5÷19 ፣ ቆላ. 1÷22 ፣ ሮሜ 5÷10) ስለዚህ አብና ወልድ ስንል በሥጋውና በመንፈሱ (በመለኮቱ) መካከል ያለውን የእግዚአብሔርን ባህርያት ያሳየናል ማለት ነው ። ክርስቶስ ለአብ መልኩ ወይም ምስሉ ነው (ቆላ. 1÷15፣ ፊል.2÷7-8) በመጀመሪያው ቃል ነበረ ሁሉ በእርሱ ሆነ..." (ዮሐ.1÷1-3)፣ መዝ.(33)÷6 "...በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ፀኑ ...."፣ ዕብ.11÷3 ".....ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ..."፣ 1ኛ ዮሐ 1÷1 ስለ ህይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውንና የሰማነውን በአይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውን እጆቻችን የዳሰሱትን እናወራለን፣ ዕብ.1÷1-3" አለማትን በፈጠረበት በልጁ (በቃሉ) በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን ....."፣ ዮሐ. 1÷14 "ቃልም ሥጋ ሆነ"፣ 1ኛ ጢሞ. 3÷16 "እግዚአብሔርን የመምሰል ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው በሥጋ የተገለጠ " ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች ወልድ በአብ ውስጥ የነበረ የአብ የራሱ ቃል የነበረ መሆኑንና በዘመን ፍፃሜ እግዚአብሔር ቃሉን ሥጋ አድርጎ እንደተገለጠ ያስተምሩናል ::

ወልድ ከአብ ውስጥ መውጣቱንም ሲያመለክት በዮሐ. 16÷28 "ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ " ብሏል (ዮሐ. 13÷3 ፣ ዮሐ. 17÷8)

ይህ የአብ ቃል በዘመኑ ፍፃሜ የሰውን ልጆች ለማዳን በዮሐ. 1÷14 እንደተፃፈው "ቃልም ሥጋ ሆነ " እግዚአብሔር በሥጋ ሰውነት ተገለጠ (1ኛ ጢሞ. 3:16)።

Scanned by CamScanner

ዕብ.10÷5 "……..መስዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ " ይላል። እግዚአብሔር ወደ ዓለም ሲገባ የሥጋን ሰውነት በማዘጋጀት እንደተገለጠ ይህ ጥቅስ ያስረዳል። ማቴ. 1÷23 "... እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው። "(ኢሳ. 7÷14) ይህ ጥቅስ በግልጽ እግዚአብሔር አብ እኛን ሰዎችን ለማዳን በመካከላችን በሰውነት መገኘቱን ያስተምራል (ዮሐ.14÷8-9)ይነበብ ።

ዮሐ. 2÷19-21 "ኢየሱስም መልሶ ፡-ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሳዋለሁ አላቸው ….እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበር "ይላል ። ይህ ቃል እግዚአብሔር አብ የሥጋ ሰውነቱን ማደሪያው መቅደስ አድርጎ ሥጋውን /አንድያ ልጁን/ በመስቀል ላይ ለሰው ልጆች ቤዛ እንዲሆን በመስጠት በሦስተኛው ቀን እንደሚያስነሳውና የራሱ የአብ ሰውነት ሆኖ እንደሚኖር የሚያሳየን ነው ።

ቆላ. 2÷9 " በእርሱ (በክርስቶስ) የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና" ይላል። ይህም መንፈስ የሆነውና የማይታየው መለኮት በሚታየው የሥጋ ሰውነት (በክርስቶስ) ማደሩን ያስተምረናል /ያመለክተናል/።

መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮ. 5÷19 "…..እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና " ማለቱ እግዚአብሔር አብ ራሱ በክርስቶስ ማለትም ባዘጋጀው ሥጋ (ወልድ) ውስጥ ሆኖ ወይም አድሮ የሰው ልጆችን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር (ቆላ. 1÷20-23 ፣ ሮሜ. 5÷10) ማለቱ ነው ።

በቆላስይስ 1÷19-22 "እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና …በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ" ይላል።

በዮሐ. 14÷ 8-9 ላይ "ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል" ለሚለው የፊልጶስ ጥያቄ ኢየሱስ ምላሽ ሲሰጥ " ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን ? እኔን ያየ አብን አይቶአል እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ ?እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን ?" ብሎ በመመለስ በሥጋው ውስጥ የተገለጠው አብ ራሱ ኢየሱስ መሆኑንና መንፈስና ሥጋን ነጣጥሎ ማሳየት እንደማይቻለው የማይለያይና የማይነጣጠል የአንዱ አምላክ የሥጋና የመለኮት ባህርይ መሆኑን አስረድቷል ።

ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ "ሕፃን ተወልዶልናልና÷ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር÷ ኃያል አምላክ÷ የዘላለም አባት÷ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል " /ኢሳ. 9÷6/ ብሎታልና ህፃኑ (ወልድ) ራሱ የዘላለም አባት /አብ/ ስለሆነ ከኢየሱስ ውጪ አብ አለ ብሎ ማሰብ ከእግዚአብሔር ጋር ያጣላልና ማስተዋሉ ይበጃል።

Scanned by CamScanner

በሉቃ. 1÷35 "መልአኩም መልሶ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፤ ስለዚህ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል "ይላል :: እግዚአብሔር በሥጋ ሰውነት ሲገለጥ ሰውነቱ "ልጅ" ተብሎ እንዲጠራ የተነገረ ትንቢት ነው ::

በዕብ. 1÷8-10 "ስለልጁ ግን :-አምላክ ሆይ ዙፋንህ እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል .....ጌታ ሆይ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማዮችም የእጅህ ሥራ ናቸው ....አንተ ግን አንተ ነህ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም " ይላል:: ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው ሰውነት የእግዚአብሔር ልጅ ይባል እንጂ እርሱ ራሱ ከጥንት ምድርን የመሠረተ አንዱና ብቻውን ፈጣሪ የሆነው ጌታና አምላክ መሆኑን ጥቅሱ በግልጽ ያስረዳል ::

በቆላ. 2÷8-9 "...እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን እንደ ሰው ወግና እንደ አለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ ፍልስፍና በከንቱ መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ :: በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና " ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሰዎች ፍልስፍና እንዳንዞር አስጠንቅቆናል::

ስለዚህ የእግዚአብሔር አብ ሙላት በወልድ ውስጥ መገለጡን ማወቅ ይኖርብናል ማለት ነው:: ለዚህም ነው በ1ኛ ዮሐ. 2÷23 " ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው " ተብሎ የተፃፈው ::

3.3. መንፈስ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረን መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ሌላ አካል ያለው አምላክ ሳይሆን የእግዚአብሔር አብ እስትንፋስ ነው (ኢዮ. 32÷8፤ ኢዮ.33÷4):: እግዚአብሔር አብ በሥፍራ የማይወሰንና የማይዳሰስ ቅዱስ መንፈስ ነው:: ቅዱስ መንፈስ የሆነው አብ /መለኮት/ ሥጋና አጥንት የለውም (ዮሐ.4÷24፤ሉቃ.24÷39) :: ከእግዚአብሔር የሚወጣው የመለኮት ቅዱስ እስትንፋስ (መንፈሱ) በየጊዜው ከአብ እየሰረፀ የሰዎችን ህይወት ያድሳል ይቀድሳል :: መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ራሱ በሰው ላይ የሚያፈሰው በሰው ውስጥ የሚሞላው ወይም ሰውን የሚያጠምቅበት እንጂ አንድ ወይም ሁለት ተብሎ የሚቆጠር ወይም ከአብ በተለየ አካል የሚወሰን አይደለም :: በዮሐ. 20÷21-22 ".....ይህንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ..." ይላል:: በኢዮ.33÷4 "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ ሁሉንም የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ " ይላል::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንፈስ በሉቃ. 24÷39 ሲመሰክር ".....በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት (አካል) የለውምና እኔን ዳሰሳችሁ እዩ አላቸው" ይለናል::

መንፈስ ቅዱስ ከሚሠራው ሥራ አንፃር በእርግብ፣ በዘይት፣ በነፋስ፣ በአውሎ ነፋስ፣ በውኃ፣ በእሳት፣ በደመና፣ በቅባት ወዘተ... ይመሰላል እንጂ በአካል ከእነዚህ አንዱንም ይመስላል ማለት አይደለም ::

Scanned by CamScanner

ይበልጥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ለመረዳት ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጥቅሶች ይነበቡ።
(ዮሐ. 4÷24 ዘፍ. 2÷7 ፤1ኛ ቆሮ. 10÷1-4 ፤ ሐዋ. 2÷1-4 ፤ ዮሐ. 7÷37-39 ፤
1ኛ ዮሐ. 2÷27 ፤ ዘዳ. 13÷20-21 ፤ መዝ. (139)÷7-12፤ ኤር. 23÷23)።

4. ዳግም ልደት ምንድነው?

በሮሜ 5÷12-17 "ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው (በአዳም) ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት እንደዚሁም ሁሉም ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ ..... በአንድ በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ" ይላል።
በዕብ. 9÷27-28 ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠብቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል" ይላል ።

ከላይ እንደተጠቀሰው በኃጢአት የወደቀውንና የዘላለም ሞት የተፈረደበትን የሰውን ልጅ ሁሉ ለማዳን ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ሞት መከራን ስለ ተቀበለ ሰዎች ሁሉ ሙሉ ደህንነትን ለማግኘት የወንጌልን ቃል በመስማት (ቃሉን በማመን) ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋቸዋል። (ማር.16÷15-16 ፤ ዮሐ.3÷3-5 ፤ሮሜ. 10÷17 ፤1ኛ ጢሞ. 1÷15-17)

ሰው በዚህች ምድር ለመኖር ከእናትና ከአባቱ /ከመጀመሪያው/ የአዳም ዘር እንደሚወለድ ሁሉ በሚመጣው ዓለም ማለትም በመንግስተ ሰማያት ለዘለዓለም ለመኖር በእግዚአብሔር አሠራር አምኖ ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ መወለድ ይኖርበታል። ይህም ዳግም ልደት ምንድን ነው ?ለሚለው ጥያቄ አጭር መልስ ነው ።
ጌታ ኢየሱስ በዮሐ. 3÷3-5 ሲናገር "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም " ካለ በኋላ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ሲያብራራ "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም "በማለት ሰው ሁሉ ዳግም ካልተወለደ በቀር ከእግዚአብሔር መንግስት ውጭ መሆኑን በመግለጽ ዳግም ልደት ከውኃና ከመንፈስ መወለድ እንደሆነ አመልክቶአል (1ኛጴጥ. 1÷23)።

Scanned by CamScanner

4.1. የውኃ ጥምቀት አስፈላጊነት

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሲሰበክ በእምነት የሚቀበል ሰው ሁሉ ለመዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጥልቅ ውሃ ውስጥ በመቀበር መጠመቅ እንዳለበት ታሉ ሲናገር "ያመነ የተጠመቀም ይድናል...." ይላል:: ማር.16፡16::
የውኃ ጥምቀት ማንኛውም ወንጌልን ያመነ ሰው ዳግመኛ የሚወለድበት፣ የሚድንበት፣ የኃጢአቱን ሥርየት የሚቀበልበት፣ በክርስቶስ መገረዝ የሚገረዝበትና ክርስቶስን የሚለብስበት የእግዚአብሔር አሠራር መሆኑን ታሉ ያስተምረናል፡
(ዮሐ.3÷3-5፣ማር.16÷16፣ ቲቶ3÷3-5፣ ቆላ.2÷11-14፣ ገላ. 3÷26-29 ፣ 1ኛ ጴጥ. 3÷20-21 ፣ ሐዋ. 2÷38)

4.2. የውሃ ጥምቀት በማን ስም?

የኃጢአትን ሥርየት ማግኘት ፀጋ ነው:: በበዓለ ሃምሳ ቀን ሐዋርያው ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልቶ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰብክ በወንጌል መልእክት ልባቸው የተነካ ያመኑ ሰዎች ለመዳን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሲጠይቁ፤ ጴጥሮስም መልሶ፡- "ንስሃ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ " አላቸው :: በዚያን ዕለት ሦስት ሺህ የሚያህሉ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ /ሐዋ 2÷38-41/::

በዚህ ቃል መሠረት የመዳንን ወንጌል ሰምተን ካመንን ልናደርገው የሚገባን የመጀመሪያው እርምጃ ንስሐ መግባት ነው:: በሉቃ.13÷1-5 "ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ " ተብሎ ተጽፎአል:: ንስሐ መግባት ማለት ስንኖርበት ከነበረው የኃጢአት መንገድ ወይም ክፉ አሳብና አካሄድ እንዲሁም የራስን ፈቃድ ከማድረግ ተመልሶ በእግዚአብሔር መንገድና ፈቃድ ለመገዛት በመወሰን መመላለስ ማለት ነው:: (ገላ. 5÷19-21 ፣ሕዝ. 18÷20-32 ፣ ምሳ. 28÷13)
ንስሐ ከገባን በኋላ በሐዋ. ሥራ 10÷48 "በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው " የተባለውና በምዕራፍ 22÷16 ደግሞ "አሁንስ ለምን ትዘገያለህ ተነሳና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ "የሚሉት ትዕዛዛት ይመለከቱናል ::
ሊታመኑበትም ሆነ ሊጠመቁበት የሚገባ ስም ኢየሱስ ብቻ ነው:: ቅዱስ ቃሉ በሐዋ. 4÷12 ላይ በግልጽ ሲያስተምር "መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" በማለት ለሰው ልጆች ሁሉ መድኃኒት ይሆን ዘንድ የተሰጠ ብቸኛ ስም የኢየሱስ ስም መሆኑን ያረጋግጥልናል (ፊል. 2÷10 ፣ ቆላ. 3÷17 ፣ 1ኛ ዮሐ. 2÷12 ፣ ሐዋ. 10÷43)::

Scanned by CamScanner

በማቴዎስ 28÷19 ላይ "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው " ተብለው በጌታ የታዘዙትን ትዕዛዝ ሐዋርያቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማጥመቅ ተፈፃሚ ከማድረጋቸው በስተቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ተብሎ የተጠመቀ እንድም ሰው እንደሌለ፤ የውኃ ጥምቀት መከናወን ያለበት ብቻውን አዳኝ በሆነው በጌታ በኢየሱስ ስም መሆኑን ቃሉ በተግባር ያስተምረናል::
(ማቴ. 1÷21፤ ሐዋ.2÷38፤ ሐዋ.8÷16፤ ሐዋ.10÷43-48 ፤ ሐዋ. 16÷30-34 ፤ሐዋ. 19÷1-5 ፤ ሐዋ. 22÷1-6)::
ሰው በራሱ ጥረትና በራሱ የፅድቅ ስራ ሊያስወግደው የማይችለውን የኃጢአት መርገም ፅዳ (የውርስ ኃጢአት) ሊያስወግድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ደሙን አፍስሶ ሞቶ ከተቀበረ በኋላ በሶስተኛው ቀን ተነሳ:: በመስቀል ተሰቅሎ ሳለ በጦር ሲወጋ የፈሰሰው ውኃና ደም ትልቅና ከበር የማዳን ኃይል እንዳለው በማመን በሰመ በጥልቅ ውኃ ውስጥ የሚጠመቅ ሁሉ የኃጢአቱን ሥርየት ስለሚቀበል ከውኃ ተወለደ ማለት ነው::
ማር. 16÷16 ፤ ሉቃ. 24÷46-47 ፤ሐዋ. 2÷38 ይመልከቱ)::

ስለዚህ ነው በቲቶ 3÷5 "እንደምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም" የሚለው:: በኢየሱስ ስም በመጠመቅ ክርስቶስን ለለበሱት ሰዎች ጳውሎስ ሲጽፍ :-".....ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው አሮጌው ነገር አልፎአል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል "ብሎአል (2ኛ ቆሮ.5÷17)::

4.3. የውኃ ጥምቀት ክርስቶስን ያስለብሳል

"የሥጋን ሰውነት በመገፈፍ÷ በክርስቶስ መገረዝ÷ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ፤ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ÷ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ"
(ቆላ. 2÷11-12) በማለት ይህ የሰው ሥራ ወይም ሥርዓት ሳይሆን ለትንሳኤ የሚያበቃን የእግዚአብሔር የማዳን አሠራር መሆኑን ይገልፃል:: ይህም ክርስቶስ ያዘጋጀው የመዳን መንገድ ነው ::

ቅዱስ ቃሉ በገላ. 3÷26-27 ".....ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና " ስለሚል ያልተጠመቀ ሰው ሁሉ በሥጋ ዓይን ለበሶ ቢታይም በነፍሱ ግን ራቁቱን ነው:: (ማቴ.22÷11-14) ስለዚህ ዳግም ልደት ክርስቶስን አስለብሶ ከዘላለም የነፍስ ራቁትነት ያወጣል ::

Scanned by CamScanner

ክርስቶስ እንደ ሞተ እንደ ተቀበረ ሞትን ድል አድርጎ እንደ ተነሳ የሰው ልጆች ሁሉ (እኛ ሁላችን) ንስሐ በመግባት ከክርስቶስ ጋር በእምነትና በጥምቀት በመቀበር ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን " የተባለው ቃል ይፈፀምልናል (ሮሜ. 6÷5 ፣1ኛ ዮሐ. 3÷2)። የጥምቀትን ምሥጢር ጥቅምና አስፈላጊነቱን ተገንዝቦ በእምነት የሚታዘዝ ማንም ቢኖር ሳይዘገይ ወዲያው መጠመቅና መዳን እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (2ኛቆሮ.6÷2፣ ማር.16÷16፣ ሐዋ. 2÷38 ፣ ሐዋ. 8÷12-13 ፣ ሐዋ. 8÷36-3፣ሐዋ.10÷43-48 ሐዋ.16÷30-34፣ ሐዋ. 19÷1-6 ፣ ሐዋ 22÷16)።

4.4. የመንፈስ ቅዱስ መላት አስፈላጊነት (ከመንፈስ መወለድ)

ሰው በዳግም ልደት ከዘላለም ሞት ዕዳ ነፃ ሆኖ የዘላለም ሕይወትን ወደሚያገኝበት የእግዚአብሔር መንግስት እንዲገባ ከውኃና ከመንፈስ መወለድ እንዳለበት የእግዚአብሔር ቃል በሰፊው ያስተምራል (ዮሐ. 3÷3-5 ፣ ቲቶ 3÷3-5) ።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለሚያምኑት ሁሉና መንፈሱን ለሚጠሙ ሁሉ የሚሰጥ የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ሲሆን አንድ ሰው በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ የሚታወቅበት ምልክቱ የሕይወት መታደስና በልሳን (በአዲስ ቋንቋ) መናገሩ እንደሆነ ቃሉ ያስተምረናል። (ሕዝ. 36÷25-27 ፣ ኢዮ.2÷28-32፣ ማቴ. 3÷11፣ ሐዋ. ሥራ 1÷5-8 ፣ ሐዋ. 2÷1-4 ፣ ዮሐ. 7÷37-39 ፣ ሐዋ. 10÷47-49)

በኃጢአትና በርኩሰት ተበክሎ የነበረውን የሰው መንፈስ በማደስና በመቀደስ ደስታ ሰላምና የነፍስ እረፍት የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን መንፈስ መቀበልም ትልቅ መለኮታዊ ጸጋ ነው። ቅዱስ መንፈሱን መሞላት የመንግስተ ሰማያት ወራሽ ለመሆናችን ማረጋገጫ ወይም ማህተም ነው (ኤፌ.1÷13-15፣2ኛ.ቆሮ.5÷5)። እንደዚሁም በቲቶ 3÷5-7 ".... እንደ ምህረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን "ይላል ።

ስለዚህ "መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ "ብሎ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል በማመን የዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን የሚያደርገን ቅዱስ መንፈሱን ተሞልተን በአዲስ ልሳን/ቋንቋ/ ስንናገር ነው። (ሐዋ. ሥራ 2÷1-4 ፣ ማር. 16÷17)።

መንፈስ ቅዱስን መሞላት የክርስቶስ ወገን ያደርገናል። "እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም።

Scanned by CamScanner

የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም። ክርስቶስ በመንፈሱ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው። ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል" ይላል። (ሮሜ 8፥9-11)።

በሮሜ 8፥26 ላይ ደግሞ "..... መንፈስ ድካማችንን ያግዛል " ይላል። እንደዚሁም በዮሐ. 4፥24 "እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" ተብሎ የተገለውን ማስተዋል ይገባል ።

እግዚአብሔር መንፈሱን ለሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደሚሰጥ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ተናግሯል (ኢዩ. 2፥28 ፣ ሐዋ. 2፥1-4 ፣ ዮሐ. 7፥37-39) ። በበዓለ ሃምሳ ቀን ቤተክርስቲያን ስትመሠረት እንዲህ ነበር ፦ "በዓለ ሃምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር" ይላል። መንፈስ ቅዱስ መሞላትና በልሳን መናገር ለሚያምን ሁሉ የሚሰጥ ጸጋ ነው (ሐዋ. 2፥17-21 ፣ማር. 16፥17)።

በማቴ. 3፥21 እንደተገለፀው በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ኢየሱስ ራሱ ስለሆነ ፊትን አይቶ የማያደላ የልብ አምላክ ነውና ለቀደሙት ቅዱሳን ሁሉ እንደሰጠ ዛሬም ላመኑትና ለሚጠሙት እንደ ፀጋው ብዛት መንፈሱን ይሰጣል (ዮሐ. 14፥16) ። ስለዚህ ቃሉን አምኖ የሚለምን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ሕይወቱ ይታደሳል ።

5. በቅድስና መኖር

ሰው ከዘላለም ሞት አምልጦ በመንግስተ ሰማያት ለዘላለም ለመኖር ዳግም ከውሃና ከመንፈስ ተወልዶ በቅድስና መኖር ይገባዋል።

ከውኃና ከመንፈስ ዳግመኛ በመወለድ የእግዚአብሔርን ልጅነት ሥልጣን ያገኘን ቅዱሳን ሁላችን እግዚአብሔርን በመምሰል ዘወትር በጽድቅና በቅድስና መኖር ይገባናል።

Scanned by CamScanner

ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ወይም የቅዱስ መንፈሱ ማደሪያ ስለሆነ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ በመራቅና በመንፃት እንዲሁም በልባችን፣ በአንደበታችን፣ በሃሳባችንና በአኗኗራችን ሁሉ ይህን ዓለም እንዳንመስልና ከኃጢአት ጋር እንዳንተባበር ቃሉ ያስተምረናል::

(1ኛ ቆሮ. 3÷16-17 ÷ 1ኛ ቆሮ. 6÷19-20 ÷ 2ኛ ቆሮ. 6÷14-18 ÷ ኤፌ. 1÷4 ÷ኤፌ. 4÷17-32 ፣ ኤፌ.5÷1-33፣ ዘዳ. 22÷5 ፣ ዘሌ. 19÷1-4 ማቴ.5÷48፣ 2ኛቆሮ. 7÷1-2 ፣ ዕብ.12÷14 1 ኛጢሞ. 2÷8-12 ፣ ኢዮ. 22÷21-30)

6. አንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን

ኢየሱስ የመሠረታት የገሃነም ደጆች የማይችሏት ቤተክርስቲያን አንዲት የማትለያይና የማትከፋፈል ቅድስት ቤተክርስቲያን በምድር ላይ አለች:: "ኤፌ.2÷11-22 ቤተክርስቲያን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ከአይሁድም፣ ከአህዛብም በደሙ ተዋጅታ አንድ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ሆና የተሠራችና እየታነጸች ያለች አንድ አካል ናት::" ኤፌ.3÷1-6 በመሆኑም አይሁድና አህዛብ በአንድ አካል (በአንዲት ቤተክርስቲያን) ሆነው አብረው ወራሾች ናቸው:: 1ቆሮ.12÷12-13 ቤተክርስቲያን አንድ አካል ብቻ በመሆኗ ከነገድ ከወገን ከቋንቋ ሁሉ የተዋጁት ምዕመናን የአካሉ ብልቶች ናቸው:: ይህች ቤተክርስቲያን በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት (ትምህርት) ላይ ተመስርታ (ታንፃ) ወንጌልን ለጠፉት ነፍሳት ሁሉ እየመሰከረች ወደ መዳን ልታመጣ ትልቅ አደራ አለባት::

(ማቴ. 16÷18 ፣ ኤፌ. 2÷20-22 ፣ኤፌ. 4÷4-6)::

Scanned by CamScanner

ማጠቃለያ

በኢሳይያስ 43÷10 "ታውቁና ታምኑበኝ ዘንድ እኔም እንደሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ ...." ብሎ መናገሩ የሰው ልጆች ሁሉ አንዱን አምላክ (በሥጋ የተገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን) አውቀው እንዲያምኑትና እንዲያመልኩት የተፃፈ ስለሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል (ኤር.6÷16፣ ዮሐ.8÷24-27)። በዮሐ. 8÷31-32 ላይ ኢየሱስ ላመኑበት አይሁድ ሲናገር "እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ-መዛሙርቴ ናችሁ እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል" ብሎአቸዋል ።

በዮሐ.1÷12-13 "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።" የሚለው ቃል እንዲፈጸምልዎ ዳግም መወለድ ይገባዎታል። "እነሆ÷ የተወደዳው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ÷ የመዳን ቀን አሁን ነው።" (2ኛ ቆሮ. 6÷2) ይላል ቅዱስ ቃሉ ።" ይህም ማለት ዳግም የመወለድ ቀን አሁን ነው ማለት ነው። ከአንድ ቀን ወይም ከአንድ ሰዓት በኋላ ምን እንደምንሆን ስለማናውቅ ልቆይ እደርስበታለሁ የሚባል አይደለም። ከቡር የሆነው የአምላክ ቃል "አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሳና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ " ይላል (ሐዋ. 22÷16)።

ከዚህ ምንም ቢደረግለት በቃኝ ከማይለውና ከማይረካው በመጨረሻም ወደ አፈር ተመልሶ ከሚገባውና ከሚበሰብሰው አዳማዊ ተፈጥሮ ወጥቶ የዘላለም ሕይወት ወደሚገኝበት ወደ ሁለተኛው አዳም /ወደ ክርስቶስ/ መጥቶ ክርስቶስን በመልበስ በሕይወት ለመኖር የመወሰኛውና በቅዱስ ቃሉ መሠረት ዳግም የመወለጃው ሰዓት አሁን ነው ። ስለዚህ እርስዎም እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት የሆነውን፣ ያለውንና የነበረውን፣ የሚመጣውን ንጉሳችንን፣ ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅና በማመን ከኃጢአትና ከዘላለም ሞት አርነት እንዲወጡ በአክብሮት ጥሪአችንን እናስተላልፋለን (1ኛዮሐ.5÷20-21 ይሁዳ ቁ.2-4)።

በመዝ.(119)÷59-60 እንደተባው እንደ ንጉስ ዳዊት " ስለ መንገዶችህ አሰብሁ እግሬንም ወደ ምሥክሮችህ መለስሁ ትዕዛዝህን ለመጠበቅ ጨከንሁ አልዘገየሁምም " የሚል ታዛዥ ልብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይስጥዎት አሜን ።

Scanned by CamScanner

ለተጨማሪ ማብራሪያ ፡-

ኢትዮጵያ ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን



4442



+251 146 63000 / +251 146 60086

+251146 53481 / +251 147 03675

E-mail: ace@ethionet.et

apchet@ethionet.et

FAX 251-1466-00-88



አዲስ አበባ ይጠይቁ

Design & Printed @ RELA P.P.0118503232/0911524040

Scanned by CamScanner